# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 228 መስከረም 17 2005 ገጽ 1


ከወያኔ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ሎሌነት ነፃ ለመውጣት መንገድ መሻት የራሳችሁ ኃላፊነት ነው። የገዛ ራሳችሁን፣ ቤተሰቦቻችሁን፣ የኦሮሞን ሕዝብ እና ኢትዮጵያን እያዋረደ፤ ሃብቷን እያዘረፈ ካለው ወያኔያዊ ኦሕዴድ ተላቀቁ። አሊያም እውስጡ ሆናችሁ ድርጅቱን ግደሉት። የኦሕዴድ መኖር ለወያኔ ካልሆነ በስተቀር ለእናንተ፣ ለቤሰቦቻችሁ፣ ለክልላችሁ ለኦሮሚያና ፣ ለኢትዮጵያ አይበጅም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቃውሞ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እየተሸጋገረ ነው፤ በምርጫው ቀን ተቃውሞዓችን በአደባባይ ይሆናል ብለዋል

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቃውሞ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እየተሸጋገረ ነው። አርብ መስከረም 18 ቀን 2005 ዓም በአንዋር መስጊድ ብቻ ግማሽ ሚሊዮን የተገመተ ሕዝብ ተገኝቶ ተቃውሞውን አሰምቷል። ከአዲስ አበባ ውጭም በተለያዩ ከተሞች ምዕመናን በከፍተኛ ቁጥር በመሰባሰብ ተቃውሞዓቸውን አሰምተዋል።

በአዲስ አበባው አንዋር መስጊድ ለአስር ደቂቃዎች ተቃውሞ ለማሰማት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ምዕመናኑ ከሠላሳ ደቂቃዎች በላይ የተደራጀ ተቃውሞ አሰምተዋል። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ቁጣ ከሌላው ጊዜ ከፍቶ መታየቱም በቦታው የነበረ ዘጋቢያችን ከላከልን ሪፖርት መረዳት ተችሎአል።

ምዕመኑ ተቃውሞአቸውን በገለጹበት ስፍራ የወያኔው አገዛዝ በርካታ ፓሊሶችና ጆሮጠቢዎችን ያሰማራ ቢሆንም ሕዝቡን ለማስፈራራት ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል። እንዲያውም ፓሊሶች አራት ሴቶችንና ሶስት ወንዶችን ይዘው ለመሄድ ሲሞክሩ ምዕመናኑ ተረባርበው አስጥለዋቸዋል።

በትናንትናው ዕለት በታየው ተቃውሞ የሙስሊሙን ቁጣ ያባባሰው በእስር ላይ በሚገኙ የሙስሊም መሪዎች ላይ የሚደረገው ድብደባና ሰቆቃ እንዲሁም ከህዝበ ሙስሊሙ ፈቃድ ውጪ የ ሃይማኖት መሪዎችን በቀበሌ ለማስመረጥ ላለፉት ሁለት ሳምንታት ካድሬዎችን ለቅስቀሳ በያንዳንዱ ቤት በመላክ ፈቃደኛ የማይሆኑትን ለማስፈራራት እየተደረገ ያለው ሙከራ እንደሆነ ታውቆአል።

አዲስ አበባ የሚገኘው የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው ወ/ሮ ሽምሲያ አህመድ የተባሉ የቤት እመቤት የቀበሌ ካድሬዎች እቤታቸው ድረስ ሂደው በቀበሌ ውስጥ በሚደረገው የማጭበርበሪያ የመጅሊስ ምርጫ ካልተሳተፍሽ የምትኖሪበት የቀበሌ ቤት ይወሰድብሻል መባላቸውን እሳቸው ግን ከነልጆቻቸው በረንዳ ላይ ቢጥሏቸውም እንኳ ምርጫው ላይ ለመሳተፍ ሲሉ ከቤታቸው እንደማይወጡ የእልህ ሲቃ እየተናነቃቸው ተናግረዋል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ሞት ተደስታችኋል የተባሉ 120 የመተማ ነዋሪዎች መታሰራቸው ተዘገበ

ልማታዊ መንግሥት ነኝ በሚል ርካሽ ፕሮፖጋንዳ አባላቱንና የጥቅም ተጋሪዎቹን አደናግሮ በመግዛት ላይ ያለው የወያኔ አገዛዝ ያለምንም ቅስቀሳና ጉትጎታ በመለስ ዜናዊ ሞት ድፍን አገር እንዳዘነ ተናግሮ ሳያበቃ ሃዘኑን አልተጋራችሁም የሚላቸውን ዜጎች እያደነ ማሰር መጀመሩ ለማወቅ ተችሎአል።

ለሞተ ሰው አለማዘን እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ዜጎችን ማሰር በተጀመረበት በዚህ የወያኔ ዘመቻ በደቡብ ያገራችን ክልል እስከ 6 ወር የሚደርስ እስራት የተፈረደባቸው እንዳሉ በተዘገበ በሁለተኛ ቀን ሰሜን ጎንደር ውስጥ በመተማ ከተማ ከ120 በላይ ሰዎች በተመሳሳይ ክስ ተወንጅለው እስር ቤት መወርወራቸው ሪፖርት ባልተጠናከረባቸው ሌሎች ክልሎች ተመሳሳይ ጥቃት እየተፈጸመ መሆኑን አመላክቶአል።

ኢሳት ያነጋገራቸውን የመተማ አካባቢ ነዋሪ ዋቢ አድርጎ እንደዘገበው በመተማ የታሰሩ ሰዎች የመለስ ዜናዊ ሞት እንደተሰማ " እንኳንም ሞተ፣ ተገላገልን" በማለት በመጠጥ ቤቶችና የተለያዩ ቦታዎች ደስታቸውን ገልጠዋል" ተብለው በመወንጀላቸው ነው።

በመለስ ዜናዊ ሞት ተደስታችኋል በሚል ተወንጅለው መተማ ውስጥ የታሰሩ እነዚህ ዘጎች በእስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ድብደባ እና ስቃይ እንደተፈጸመባቸው እንዲሁም ይህ ዜና እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ ፍርድ ቤት አለመቅረባቸውም ታውቋል።

ወያኔ 14 ቀን የፈጀ የግዴታ ሃዘን ቀን በመላው አገሪቱ ባወጀበት ሰሞን በሰሜን ጎንደር በሚገኙ እያንዳንዱ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከ200 እስከ 400 የሚደርሱ የኢህ አደግ አባላት ተልከው ሃዘናቸውን እንዲገልጹ ተደርገኦ እንደነበር በዚያው በሰሜን ጎንደር በጃን አሞራ ወረዳ የሚገኙ አንድ የኢህ አደግ ባለሥልጣን ለ ኢሳት መግለጻቸውን ኢሳት በዘገባው አክሎ ገልጾአል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የሰሜን ሱዳንና ደቡብ ሱዳን መሪዎች በመካከላቸው የተፈጠረውን ግጭት ለማስወገድ በተፈራረሙበት የስምምነት ስነ ስርዓት ላይ አምባገነኑን መለስ ዜናዊን በመተካት በረከት ስምኦን መገኘቱ ተነገረ

የበረከት ስምኦን በዚህ ስነ ስርዓት ላይ በኦፊሴል መገኘት በወያኔ-ኢህአዴግ ውስጥ ከተከፋፈሉት ቡድኖች ለጊዜውም ቢሆን የበረከት ቡድን በአሸናፊነት እየወጣ መሆኑን የሚያሳይ ነው ተብሏል።

ከዚህ በፊት አንድም ጊዜ እንዲህ ዓይነት ስነስርዓቶች ላይ ታይቶ የማያውቀው በረከት በዚህ ወቅት በዚህ ስፍራ መገኘቱ ከሀይለማሪያም ደሳለኝ የይስሙላ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ጀርባ የፖለቲካ ጨዋታውን እየተጫወተ ያለው እርሱ መሆኑን አመላካች ነው ሲሉ ዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የፖለቲካ ባለሙያዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል ሃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብሎ ከተመደበ ሳምንት ያለፈው ቢሆንም እስካሁን መለስ ዜናዊ ለ21 አመታት ይዞ ወደ ቆየው ታላቁ ቤተመንግስት መግባት እንዳልተፈቀደለት ለማወቅ ተችሎአል።ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አዜብ መስፍን አልወጣም ብላ የሙጢኝ ማለቷ እንደሆነ ከታማኝ ምንጮች የደረሱን መረጃዎች አረጋግጠዋል።

መለስ ዜናዊ በሞት ከተለያቸው ወዲህ በመለስ ሥም መማልና መገዘት የጀመሩት ኢህአደጋዊያን ወያኔዎች አዘብ መስፍንን ለ21 አመት ከኖረቺበት ግቢ በሃይልም ሆነ በሥነሥር ዓት ለማስወጣት ድፍረት ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ ባይጠበቅም እራሷ አዜብ መስፍን ሃሳቧን ለውጣ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ብትሆን በመጀመሪያ ቀን የጠቅላይ ምንስቴርነት ንግግሩ " ዘላልማዊ ግርማና ሞገስ ለታላቁ መሪያችን ይሁን " በማለት አምልኮ መለስ የጀመረው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ለዚህ ማዕረግ ያበቃው አለቃው ምስቲ በወጣችበት ቤት ውስጥ ገብቶ ለመኖር ድፍረትና ወኔው ይኖራዋል ወይ የሚል ጥያቄ አስነስቶአል።

አዘብ መስፍን መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ከመቶ ሚሊዮን በላይ የመንግሥት ገንዘብ ወጪ በማድረግ ምንሊክ ቤተመንግሥት ውስጥ እያሳነጸ መሆኑ ተዘግቦ ወደ ነበረው ህንጻ እንድትዛወርና አሮጌውን ህንጻ ለሃይለማሪያም ደሳለኝ ልትሰጠው እንደምትችል ለቤተመንግሥቱ ቅርብ የሆኑ አንድ ምንጭ ለዝግጅት ክፍላችን ፍንጭ ሰጥተዋል።

አዜብ መስፍን የባሌበቷን ሥልጣን መከታ በማድረግ በዘረፈቺው የአገር ሃብትና ገንዘብ አገሪቱ ውስጥ አትራፊ በሚባሉ የንግድ ድርጅቶች ሁሉ ውስጥ እጇን አስገብታ በብርሃን ፍጥነት ለመክበር ከበቁ ጥቂት የዘመኑ የናጠጡ ዲታዎች ተርታ መሰለፏን ከአመት በፊት ስፔን ውስጥ የሚታተም ጋዜጣ ዘግቦ እንደነበር አይዘነጋም። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በደቡብ ክልል "መለስ ዜናዊ እንኳን ሞተ" ብለው ተናግረዋል የተባሉ በርካታ ሰዎች መታሰራቸው ታወቀ

ወያኔ በመላው አገሪቱ ያሉ ዜጎች በግዴታ ለመለስ ዜናዊ ሃዘን እንዲቀመጡ በተዋረድ ባሉ መንግሥታዊ መዋቅሮች ያስተላለፈውን ትዕዛዝ አላከበሩም የተባሉ በርካታ ሰዎች መታሰራቸውንና በደቡብ ኦሞ ዞን በደቡብ አሪ ወረዳ የሚገኙ 4 አርሶአደሮች፣ "መለስ ዜናዊ እንኳንም ሞተ፣ አናዝንም" በማለት ሲናገሩ ተሰምተዋል በሚል ክስ እንደተመሰረተባቸው ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ማስረጃ አረጋገጠ።

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች መስተዳደር ክልል የኦሞ ዞን አሪ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ማህተም ያለበት ይህ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው የክስ ቻርጅ እንደሚያመለክተው አርሶ አደሮቹ በኢፌዲሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 4 /86 ሀ ላይ የተደነገገውን ተላልፈዋል የሚል ሲሆን የክሱ ጭብጥ "ተከሳሾቹ በነሃሴ 18 ቀን 2004 ዓም እለቱ አርብ ጧት 3 ሰአት ላይ በጎይዳመር ቀበሌ ውስጥ አቶ ገዛሀኝ ሀሞሾ ቤት ውስጥ ሀዘንተኛ ለማጽናናት በተሰበሰቡበት 4ቱም ተከሳሾች አንድ ላይ ሆነው "መለስ እንኳን ሞተ አናዝንም፣ መንግስት ሞቷል፣ መንግስት የለም" በማለት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው መንግስት እንደሌለ በማሰብ ህዝብ ለማናወጥ በሚችል ሁኔታ ህዝብን በማሳሳት ወንጀል" ፈጽመዋል የሚል ነው።

የወያኔ መሪዎችና አፈቀላጤዎቻቸው እየተቀባበሉ ህዝብ ያለምንም ግዴታና ጉትጎታ በነቂስ ወጥቶ ለልማታዊው ጠቅላይ ምንስቴሩ ለቅሶ አነባ በማለት ያለመታከት ርካሽ ፕሮፖጋንዳቸውን ሲነዙ የከረሙ ቢሆንም በገሃድ ያለው ሃቁ የሚያመለክተው ግን ቀብሩ ከተፈጸመ በኋላም ቢሆን ሃዘኑ አይመለከተንም ያሉትን መወንጀል፤ ማሰርና ማዋከብ ሆኖአል።

ለመለስ ዜናዊ አለማዘን በወንጀል እንደሚያስከስ ስ ይፋ በሆነው የክስ ቻርጅ ከተመለከተው በተጓዳኝ በዚያው በደቡብ ክልል ሸንቃማ ቢሊ፣ ሸንጋማ ወሰት፣ ሌጠር፣ አመር፣ ጉመር፣ አይዳና ከነአመር ከሚባሉ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ

## ጥሪ ለኦሕዴድ አባላት!!!

### ተዋርዶ ከማዋረድ መላቀቂያችሁ አሁን ነው!!!

የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) ታላቁን የኦሮሞ ሕዝብ እወክላለሁ ይላል። ኦሮሞ ደግሞ የኢትዮጵያ ምሰሶ ነው። ከዚህ ታላቅ ሕዝብ ወጣሁ የሚለው ኦሕዴድ ግን እወክለዋለሁ የሚለውን ሕዝብ ጥቅም ሊጠብቅና ሊያስጠብቅ ቀርቶ ለራሱ እንኳን መሆን ያልቻለ፤ የተናቀና የተዋረደ የወያኔ ሎሌ ሆኖ ድፍን 21 አመት አስቆጠሮአል። ወያኔ ደግሞ ስሙ እንደሚያለክተው ከውልደቱ ጀምሮ የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት ነው።

ወያኔ ትግራይን “ነፃ” ካወጣ በኋላ ለመቋቋሚያ የሚሆነው ግዛት አስፈለገው። ወያኔ ኦሮሚያን መግዛትና መበዝበዝ ለሕልውናው አስፈላጊ እንደሆነ ተገነዘበ፤ ለዚህም ተንቀሳቀሰ። በኦሕዴድ ሎሌነት የኦሮሚያን ሕዝብና መሬት በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። “ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ” እንዲሉ በዘር ፌደራሊዝም ስም የኦሕዴድ ካድሬዎች ኦሮሚያን ለወያኔ ዘረኞች አሳልፈው ሰጧት። ኦሕዴድ ባይኖር ኖሮ ኦሮሚያ የወያኔ መፈንጫ ባልሆነችም ነበር። የኦሕዴድ ክህደት ግን በዚህ አላበቃም። የወያኔ ሹማምንት በኦሮሞ ለም መሬት፣ ደን፣ ማዕድንና ውሃ ሲከብሩ የኦሕዴድ ሎሌዎች ለፍርፋሪ ሲሉ ብዘበዛውን ማሳለጥ ጀመሩ። የኦሕዴድ ካድሬዎች የገዛ ወገናቸውን አሳረዱ፤ ያደጉበትን መንደር፤ የሮጡበትን ሜዳ አዘረፉ።

በኦሕዴድ ሎሌነት ሳቢያ ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ እስር ቤቶች በኦሮሞዎች ተሞልተዋል። የኦሮሞ ለም መሬቶች ለወያኔና የወያኔ ወዳጆች ለሆኑ ባዕዳን በብላሽ ታድሏል። የኦሮሞ ደኖች ተመንጥረዋል። የኦሮሞ ማዕድናት ወያኔ እንዳሻው የሚያፍሰው ባላቤት ያጣ ንብረት ሆኗል። በኦሕዴድ ሎሌነት ሳቢያ ዛሬ የኦሮሞ ገበሬ ብቻ ሳይሆን የዱር አራዊቱም ተሰደዋል። ይህ ሁሉ የሆነው የኦሮሞ ልጆች ነን በሚሉ የኦሕዴድ ካድሬዎች ሎሌነት መሆኑ እጅግ የሚያስቆጭና የሚያንገበግብ ነገር ነው።

አሁን ደግሞ የባሰ አሳፋሪ ነገር እየታዘብን ነው።

ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በመሞቱ በረከት ስምኦንና ግንባር ቀደም ወያኔ ደቀመዛሙርቱ የወታደሩንም የሲቪሉንም ሥልጣን እየተቀራመቱ ነው። እስቲ እንጠይቅ።

- ከዚህ ቅርምት ለኦሕዴድ ምን ደረሰው? ምንም።
- የጄኔራልነት ማዕረግ ለሕወሓት ሰዎች ሲታደል ኦሕዴድ ምን አደረገ? ምንም።
- የአገሪቱ የደህንነት መዋቅር ሙሉ በሙሉ በወያኔ ሲያዝ ኦሕዴድ ምን አለ? ምንም።
- የአገሪቷ ንብረት በሙሉ ወያኔ በፈለፈላቸው ድርጅቶች ሲያዝ ኦሕዴድ ምን አለ? ምንም።

ሟቹን መለስ ዜናዊን ለመተካት በነበረው ሽኩታ የኦሕዴድ ሚና ምን ነበር? ምንም።

ይህ ከምር ያሳፍራል።

አሳፋሪነቱ ደግሞ ለኦሕዴድ አባላት ብቻ ሳይሆን ለመላው የኦሮሞ ሕዝብ ከዚያም አልፎ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተርፎአል ። የኦሮሞ ሕዝብ ኦሕዴድን የመሰለ አሳፋሪና ከሃዲ ድርጅት በታሪኩ ገጥሞት አያውቅም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ኦሕዴድን ከአባላቱ ለይቶ ማየት ይሻል። ከዚህም በተጨማሪ የኦሕዴድን ከፍተኛ አመራር አባላትን ከበታቾቹ ለይቶ ይመለከታል። ሥጋቸውን ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውንም ሳይቀር ለወያኔ አሳልፈው የሰጡ ሰዎች ኦሕዴድ ውስጥ መኖራቸው ምንም ጥርጥር የለውም። በአንፃሩ ደግሞ ራሳቸውን ከወያኔ ባርነት ነፃ አውጥተው የበደሉትን ሕዝብ በመካስ ላይ ያሉ ጀግኖች መኖራቸው ግልጽ ነው። ግንቦት 7፡ ከውስጥ ሆነው ወያኔን እየታገሉ ላሉም ሆነ ድርጅቱን ጥለው የነጻነት ትግሉን ለተቀላቀሉ ለእነዚህ ቆራጥ የቀድሞ የኦሕዴድ አባላት፤ የዛሬ አርበኞች ትልቅ አክብሮት አለው። በሚያደርጉት ትግልም ከጎናቸው ቆሟል፤ ወደፊትም ይቆማል።

ግንቦት 7፣ ብዙሃኑ የኦሕዴድ አባላት ራሳቸውን ከወያኔ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ነፃ የማውጣት የግል፣ የወገንና የአገር ግዴታ አለባቸው ብሎ ያምናል።

ስለሆነም ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለብዙሃኑ ኦህዴድ አባላት የሚከተለው ጥሪ ያደርጋል።

የኦሕዴድ አባላት ሆይ!

ከወያኔ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ሎሌነት ነፃ ለመውጣት መንገድ መሻት የራሳችሁ ኃላፊነት ነው። የገዛ ራሳችሁን፣ ቤተሰቦቻችሁን፣ የኦሮሞን ሕዝብ እና ኢትዮጵያን እያዋረደ፤ ሃብቷን እያዘረፈ ካለው ወያኔያዊ ኦሕዴድ ተላቀቁ። አሊያም እውስጡ ሆናችሁ ድርጅቱን ግደሉት። የኦሕዴድ መኖር ለወያኔ ካልሆነ በስተቀር ለእናንተ፣ ለቤሰቦቻችሁ፣ ለክልላችሁ ለኦሮሚያና ፣ ለኢትዮጵያ አይበጅም። በአሁኑ ሰዓት የወያኔን እድሜ እያራዘማችሁ ያላችሁ እናንተ ናችሁ። በፓርላማው ሳይቀር ለወያኔ የማሳሳቻ ጭንብል የሆናችሁለት እናንተ ናችሁ። ተዋርዳችሁ ሕዝባችሁን አታዋርዱ። ይልቁንስ ታሪክ ሥሩ። ዛሬውኑ የነፃነት ትግሉን ተቀላቀሉ።

አለበለዚያ ወያኔ ያለበሳችሁን የውርደት ካባ ለማውለቅ እንኳን ጊዜ አይኖራችሁም።

**መልካም አዲስ ዓመት!!!**

## ኢትዮጵያ የኢንተርኔትና የዲጂታል ሚዲያ ነጻነት በእጅጉ እያቀለቀለ ከሄደባቸው በጣት የሚቆጠሩ ሀገራት አንዷ መሆኑዋን ፍሪደም ሀውስ የተባለ ድርጅት ይፋ ባደረገው ጥናት አስታወቀ

ድርጅቱ "ፍሪደም ኦን ዘኔት 2012" በሚል በኢንተርኔትና በዲጂታል ሚዲያ ላይ ባደረገው ጥናት እንደገለጸው ጥናቱን ያካሄደው በአርባ ሰባት ሀገሮች ላይ ነው። ከነዚህ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በታች የሚገኙ ሰባት የአፍሪካ ሀገራት ይገኙበታል።

ጥናቱ ካካተታቸው ከሰሃራ በታች ከሚገኙት ሀገራት ደቡብ አፍሪካንና ኬንያን ነጻ የኢንተርነትና የዲጂታል ሚዲያ ያለባቸው ሀገራት ሲላቸው ናይጄሪያ፣ ዩጋንዳ፣ ሩዋንዳና ዚምባቡዌን በከፊል ነጻ፣ ኢትዮጵያን ደግሞ ጨርሶ ነጻ የኢንተርኔትና የዲጂታል ሚዲያ የሌለባት ብቸኛ ሀገር ብሏታል።

ሌላዋ በጥናቱ ከተካተቱ አርባ ሰባት ሀገራት አንዷ ቻይና ስትሆን፣ በአፈና ከተጠቀሱት ዋነኛ ሀገራት ተርታ ከፊት ተመድባለች።

ቻይና ታዲያ አፈናውን ለራሷ ብቻ አላስቀረችም፤ ይልቁኑም ለብዙዎቹ ፈላጭ ቆራጭ መንግስታት የአፈና ስልቷ ሞዴል ከመሆኑም ሌላ ኢትዮጵያን፣ ሊቢያን፣ ዚምባቡዌን፣ ስሪላንካንና ኢራንን ወደመሳሰሉ ሀገራት ባለሙያዎቿን በመላክ፣ መንግስታቱ የተቃዋሚዎቻቸውን ድምጽ ማፈን የሚያስችላቸውን ሳንሱር የማድረግና የመቆጣጠር ቴክኒካዊ አቅም ያዳብሩ ዘንድ ያልተቆጠበ ድጋፍ ታደርጋለች እንደ ጥናቱ።

ኢትዮጵያን ለመሳሰሉ አፋኝ ሀገራት እገዳና ሳንሱር ዋነኛ የተቃዋሚዎቻቸውን ድምጽ ማፈኛ ስልቶች ቢሆኑም አሁን አሁን ግን ሌሎችንም ዘዴዎች እየተጠቀሙ ይገኛሉ የሚለው ጥናቱ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ግልጽነት የጎደላቸው ህጎች ማውጣት፣ አሳሳችና አደናጋሪ መረጃዎችን መልቀቅ፣ በብሎገሮች ላይ አካላዊ ጥቃት ማድረስንና በጸሃፊዎች ላይ የማያቋርጥ ክትትል ማድረግና ወከባ መፈጸምን እንደ ተጨማሪ ስልቶች ያነሳል።

በኢትዮጵያ ለምሳሌ ታዋቂው ብሎገር እስክንድር ነጋ ለፖለቲካ ነጻነት ጥሪ የሚያስተላልፉ ጽሁፎችን በኢንተርኔት በመልቀቁ ጸረ-ሽብር በሚባል ህግ ተከሶ አስራ ስምንት ዓመት ተፈርዶበታል በማለት በማስረጃነት ጠቅሶታል።

ከዚህም ሌላ የሀሰት ዘገባ እያዘጋጁ በኢንተርኔት ለሚያሰራጩና የዜጎችን የግል የኢንተርኔት አካውንት ሰብረው ለሚገቡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ክፍያ፣ ከፍተኛ ገንዘብ ከሚከሰክሱ ሀገራት ኢትዮጵያ ግንባር ቀደሟ መሆኑዋንም አስረድቷል።

በተጨማሪም፣ ኢትዮጵያ ጥቂት የኢንተርኔት ተጠቃሚ ያለባትና እንግዳ በሆነ ሁኔታ ቴክኖሎጂውን ከማስፋፋቷ በፊት ከፍተኛ አፈና የምታካሂድ ሀገር ናት ሲል አስቀምጧታል-ጥናቱ።

ዓለማችን ዛሬ ሲሶ የሚሆነው ነዋሪዋ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ነው። ከዚህ የሚልቀው ደግሞ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተገልጋይ ነው።ከነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በርካታ ትሩፋቶችን አግኝቷል። ከየትኛውም የዓለም ጥግ መረጃዎችን በቀላሉ ያገኛል። የተቀላጠፉ የንግድ ተግባራትን ያከናውናል። እርስ በእርሱ የሰመረ ግንኙነት ያደርጋል-ሌላም ሌላም። ይሁንና ተክኖሎጂው ለፖለቲካ ለውጥ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ የሚያስበረግጋቸው መንግስታት እገዳና ቁጥጥን ጨምሮ ሌሎች የአፈና ርምጃዎች እየወሰዱበት ይገኛሉ። ከነዚህም ሃገራት አንዷ ኢትዮጵያ ናት።

## በደቡብ ክልል "መለስ ዜናዊ እንኳን ሞተ" ብለው ተናግረዋል የተባሉ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ቀበሌዎች 80 የሚሆኑ አርሶ አደሮች ለመለስ ዜናዊ ሞት አላዘናችሁም ተብለው ወደ ጋዘር ፖሊስ ጣቢያ ተወስደው አብዛኞቹ ከሳምንታት እስር በሁዋላ ክሳቸው ተቋርጦ በከፍተኛ መስጠንቀቂያና በገደብ የተለቀቁ መሆኑን ኢሳት በትናንትናው የዜና ዘገባው ይፋ አድርጎአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ በዚሁ ምክንያት ታስረው ሳይፈቱ ከቀሩት መካከል አቶ ገረሱ ጭሊ የተባሉ የአንድነት ፓርቲ አባል ከስምንት ቤተሰቦቻቸው አባላት ጋር ታስረው ከቆዩ ቦኋላ እርሳቸውና አንድ ወንድ ልጃቸው የስድስት ወራት እስር ተፈርዶባቸዋል።

# እውነት ብቻ አርነት ታወጣችኋለች!!!

በግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 221 ወጥቶ የነበር ርዕስ አንቀጽ

ከጀርመን ዘረኛ ናዚዎች ጭፍጨፋ ከሞት ከተረፉ ብዙ ዓመታት በኋላ የኖቤል የሰላም ሽልማት ተሸላሚ የሆኑት ኤል ዊይሰል እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር በአፕሪል 12 1999 የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተንና ባለቤታቸው ሂላሪ ክሊንተን በተገኙበት ጉባኤ ላይ በዓለም ታላላቅ ንግግሮች ከሚባሉት አንዱን አደረጉ። የንግግራቸው ጭብጥ "እኔን ምን አገባኝ" እያሉ ከትግል መሸሽ ስለሚያስከትለው አደጋ ነበር።

ኤሊ ዊይሰል በዚህ ንግግራቸው ካሉት ጥቂት ብቻ እንጥቀስ

*በብርሃንና በጨለማ፤ በምሽትና በቀን፤ በወንጀልና በቅጣት፤ በጭካኔና በፍቅር፤ በጥሩና በመጥፎ መካከል ግድ የሌለው ሰው መሆን ተፈጥሮዓዊ አይደለም"። ጎረቤቶቻቸው ሲበደሉ፣ ሲገረፉና ሲደገሉ እያዩና እየሰሙ ራታቸውን በልተው፤ ወይን ተጎንጭተው በሰላም እንቅልፋቸውን የሚተኙ ሰዎች ጤነኞች ሰዎች አይደሉም።*

*እርግጥ ነው በሌላ ሰው ስቃይ ውስጥ ጣልቃ መግባት በራስ ላይ ስቃይን መጋበዝ ስለሚሆን "ምን አገባኝ" ቀላል መሸሻ ነው። ሆኖም ግን ይህ "ምና አገባኝ" ነው እኛን ከሰውነት ተርታ የሚያወጣን። ….. "ምን አገባኝ" ከግልጽ ጥላቻ የከፋ ነው።*

ግዴለሽነት ፈጽሞ ሰውኛ ነገር አይደለም።

የኤል ዊይሰል ንግግር ያተኮረው በጀርመን ናዚ ወቅት ብዙዎች ባሳዩት ግዴለሽነት የደረሰውን ጥፋት ለማመልከት ቢሆንም ከዚያ ጊዜ ወዲህ "ምን አገባኝ" የአምባገነኖች ምሽግ ሆኖ ቆይቷል።
እኛም አገር ውስጥ "እኔን ምን አገባኝ" የሚሉ ብዙ ሰዎች ባይኖሩ ኖሮ የትግራይ ገዢ ጉጅሌ "ጭብጥ በማይሞሉ" ጥቂት ሰዎች ታግዞ እንዲህ እንዳሻው ባልፈነጨብንም ነበር። የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ጉልበት የሰጠው የብዙ ሰዎች "እኔን ምን አገባኝ" የሚለው ሽሽት ነው።

- ወገኖቻችን ሲረገጡ፣ ሲሰደዱ፣ ሲታሰሩ፣ ሲደበደቡ፣ ሲጋዙ፣ ሲሰደቡ፣ ሲገደሉ እያየን፤ መናገርም መስማትም ወንጀል ሆኖ ሲያስቀጣ እየታዘብን እንዴት አስችሎን ዝም እንላለን?
- ገዢዎችና ምስለኔዎቻቸው በህንፃ ላይ ህንፃ፤ በሃብት ላይ ሃብት ሲጨምሩ እያየን እኛ የእለት እንጀራ ማጣታችንን እንዴት ተቀብለን እንኖራለን?
- ለጋ ኮረዳዎች ለቤተሰቦቻቸው ስንቅና ልብስ የሚሆን ጥሪት ለማፍራት ለአረብ አገራት ግርድና ሲሸቀዳደሙ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ልጃገረዶች ለግርድና ወረፋ ሲጠብቁ እያየን እንዴት አስችሎን ዝም እንላለን?
- ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች ቁራሽ መሬት አጥተው ለቀን ሠራተኝነት ደቡብ አፍሪቃ ድረስ በእግራቸው ለመሄድ ከሠፈራቸው ነቅለው ሲነሱ ለአረብና ቻይኛ ቱጃሮች ከመቶ ጋሻ በላይ ለም መሬት ሲሰጥ እያየን እንዴት አስችሎን ዝም እንላለን?
- ገዳሞቻችን እና መስጊዶቻችን ሲደፈሩ እንዴት ዝም እንላለን?
- ሰላማዊ ዜጎች "ሽብርተኛ" እየተባሉ ሲፈረድባቸው እያየን እና እየሰማን እንደምን ዝም እንላለን?
- ጥቂቶች በዘራቸው እየተመረጡ ሲሾሙና ሲሸለሙ፤ ብዙሃን ደግሞ በዘራቸው ምክንያት ሲሰደቡ፣ ሲዋረዱ እና ሲበደሉ እያየን እንዴት ዝም እንላለን?
- የመንግሥት ስልጣን እና ሃብት በዘር መስፈርት ሲታደል እያየን እንዴት አስችሎን ዝምታን እንመርጣለን?
- ጥቂቶች ብዙሃንን ባርያ አድርገው ሲገዙ እያየን ዝም ስንል እኛ ራሳችን ለባርነት መስማማታችን እንደሆነ እንዴት ይጠፋናል?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ ግዴለሽነት ማብቃት አለበት ይላል።

ትግላችን የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እየተዳረሰ ነው። የሁላችንም ትኩረት የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የጫነብንን ይህን አስከፊ ዘረኛ ሥርዓት ማስወገድ መሆኑን ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። ይህ ሥርዓት መሠረቱ ተንዷል። በዚህ ወቅት ገለልተኛ መሆን፤ በዚህ ወቅት ግዴለሽ መሆን ከሰውነት ተርታ መውጣት ነው።

እስካሁን "እኔ ምን አገባኝ" ስትሉ ለቆያችሁ ወገኖቻችን በሙሉ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የሚከተለውን ጥሪ ያስተላልፋል።

የነፃነት ትግልን "በምን አገባኝ" መሸሽ ለጠላት ከመገበር ተለይቶ አይታይም። ስለሆነም ሳይዉል ሳያድር ትግላችንን ተቀላቀሉ!!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በመለስ ዜናዊ ፍቅር የታወረ አንድ ወጣት እራሱን ከ 10ኛ ፎቅ ወርውሮ ገደለ ሲል ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ

በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ከ200 በላይ ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች በጠራራ ጸሃይ በተጨፈጨፉበት አዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የነበረ የ30 ዓመት ወጣት የመለስ ዜናዊ ህልፈት የፈጠረበትን ሃዘን መቋቋም ተስኖት እራሱን ከ10 ፎቅ ላይ ወርውሮ እንደገደለ ሪፖርተር ጋዜጣ መስከረም 13 ባወጣው እትሙ ዘገበ።

እንደ ሪፖርተር ዘገባ በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ በሾፈሪነት ሥራ ተቀጥሮ ይሰራ እንደነበር የተገለጸውና ለመለስ ዜናዊ ሲል እራሱን አጠፋ የተባለው ወጣት ኪስ ውስጥ ለሕይወቱ መጥፋት ምክንያት "ባለራዕዩ፣ ለወጣቱ በተለይ ሥራ ሌለው ትኩስ ኃይል እንዴት ሥራ መፍጠር እንደሚችል በተግባር ያሳዩ፣ ሁሉም የሰው ልጆች እኩል መሆናቸውንና በረሀብና በእርዛት የምትታወቅን አገር መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ ባደረጉት ጥረት ከፍተኛ እመርታ ያሳዩት ጠቅላይ ሚኒስትር ከሞቱ፣ "መኖር ለምን ያስፈልጋል" የሚል ጹሁፍ ተገኝቶአል ተብሎአል።

የዝግጅት ክፍላችን ይህንን የሪፖርተር ዘገባ ለማጣራት ያደረገው ሙከራ ውጤት ገና ያልደረሰ ቢሆንም ዜናው የፈጠራ ይሁን የእውነት ብዙ ሰዎችን እያነጋገረ ነው። ምክንያት በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘመን አገሪቷ ውስጥ በተስፋፋው ዘረፋ፤ ሙስናና ዘርን መሰረት ባደረገ መጠቃቀም ከትቢያ ተነስተው በአንድ ጀንበር የናጠጡ ከበርቴዎች ለመሆን ከበቁት አንዳቸውም ለባለውለታቸው ህይወታቸውን ሳይሰጡ በግለሰብ ድርጅት ውስጥ በሾፌርነት የሥራ መደብ ተቀጥሮ የድህነት ኑሮ የሚገፋ አንድ ተራ ሚስኪን ዜጋ የሰቆቃው መሰረት የሆነው መለስ ዜናዊ ህልፈት በምን ተአምር ተስፋውን አጨልሞ እራሱን ለመግደል ሊያበቃው እንደሚችል ግልጽ ሊሆን ባለመቻሉ ነው ተብሎአል።

ሪፖርተርና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በተለዋወጡት መረጃ በመለስ ዜናዊ አድናቂነት ተለክፎ እራሱን አጠፍቶአል የተባለው ወጣት፤ የመለስ ዜናዊ ቱርፋት ነው ያላቸው ለወጣቱ የተፈጠሩ የሥራ ዕድሎችም ሆነ አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ የማሰለፍ ብቃቱ አንድም ተጠቃሚ እንዳልነበረ የሚያረጋግጠው አስገራሚው ነገር ወጣቱ ኑሮውን የሚደጉመው በሾፌርነት ሥራ በሚያገኛት ዝቅተኛ ገቢ መሆኑ በዘገባው መካተቱና ፍቅረኛው የተባለቺው እጮኛው ደግሞ ተስፋቸው ጨልሞ ወደ አረብ አገር በግርድና ለመሰቃየት ከተሰደዱ አንዷ መሆኗ መጠቀሱ ነው።

የሪፖርተር ጋዜጣ አዘጋጅና ባለቤት የሆነው አማረ አረጋዊ እራሱ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአጭሩ ከከበሩ ምርጥ የህወሃት አባላት አንዱ ሆኖ ሳለ ለዚህ የተደላደለ ኑሮ ያበቃው የቀድሞ የትግል ጓዱና አለቃው በድንገተኛ ሞት ሲቀጠፍ እራሱን ሳያመው እንዴት አንድ ሚስኪን ሾፌር እራሱን ለመለስ ሲል ገደለ ብሎ ለመዘገብ እንደደፈረ አልታወቀም።

## የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቃውሞ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እየተሸጋገረ ነው፤ በምርጫው ቀን ተቃውሞዓችን … (ከገጽ 1 የዞረ)

ወጣት አህመድ ሲራጅ ደግሞ "እኛ ነፃነት የተነፈግን ዜጎች ነን። የምርጫው እለት ተቃውሞዓችን የምናሰማው በመስቀል አደባባይ ነው። ይህ ቀን በኢትዮጵያ አዲስ የትግል ምዕራፍ የሚጀመርበት ቀን ይሆናል። በኢትዮጵያዊነታችንም በሙስሊምነታችንም ድርብርብ በደሎች ይደርሱብናል። ይህንን በደል ከትካሻችን ማውረድ የኛ ተግባር ነው። በመስቀል አደባባይ ላይ በምናደርገው ተቃውሞ ክርስቲያን ወንድሞቻችን ከጎናችን እንደሚሰለፉ እርግጠኞች ነን። እስካሁንም ከጎናችን ነበሩ። ወደፊትም እስከ ነፃነት አብረን እንዘልቃለን" ብሏል።

ወጣት ሃኒያ አህመድ ደግሞ "በአደባባይ በምናደርገው ተቃውሞ የሚመጣብንን ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ ነን። በበኩሌ ለዲኔ፣ ለእምነቴ፣ ለመብቴ ብሞት ደስተኛ ነኝ" ብላዋለች ለሪፓርተራችን።
በደሴ፣ በከሚሴ፣ በድሬዳዋና ሐረር፣ በአርሲ እና በሌሎችም የአገሪቱ ከተሞች የይስሙላ ምርጫ ይደረጋል በተባለበት የሚቀጥለው እሁድ ሙስሊሞች አቅራቢያቸው ወደሚገኘው አደባባይ ለተቃውሞ እንደሚያመሩ እየተነገረ ነው።

ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ቢሞትም አንዳችም ለውጥ ሳይደረግ አገዛዙ የቀጠለ በመሆኑ ይህ ሥርዓት ካልተወገደ በስተቀር ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖትም ሆነ የዜጎች መብቶች ይከበራሉ ማለት ዘበት መሆኑን ብዙዎች የተስማሙበት ጉዳይ ሆኗል።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ ፍትሃዊ ጥያቄ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጥያቄዓቸው የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ በመሆኑ ነፃነትና መብት የጠማው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ እንዲቆም ጥሪ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል።

## የሰሜን ሱዳንና ደቡብ ሱዳን መሪዎች በመካከላቸው የተፈጠረውን ግጭት ለማስወገድ በተፈራረሙበት የስምምነት ስነ ስርዓት ላይ አምባገነኑን መለስ ዜናዊን በመተካት በረከት ስምኦን መገኘቱ ተነገረ

የበረከት ስምኦን በዚህ ስነ ስርዓት ላይ በኦፊሴል መገኘት በወያኔ-ኢህአዴግ ውስጥ ከተከፋፈሉት ቡድኖች ለጊዜውም ቢሆን የበረከት ቡድን በአሸናፊነት እየወጣ መሆኑን የሚያሳይ ነው ተብሏል።

ከዚህ በፊት አንድም ጊዜ እንዲህ ዓይነት ስነስርዓቶች ላይ ታይቶ የማያውቀው በረከት በዚህ ወቅት በዚህ ስፍራ መገኘቱ ከሀይለማሪያም ደሳለኝ የይስሙላ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ጀርባ የፖለቲካ ጨዋታውን እየተጫወተ ያለው እርሱ መሆኑን አመላካች ነው ሲሉ ዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የፖለቲካ ባለሙያዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል ሃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብሎ ከተመደበ ሳምንት ያለፈው ቢሆንም እስካሁን መለስ ዜናዊ ለ21 አመታት ይዞ ወደ ቆየው ታላቁ ቤተመንግስት መግባት እንዳልተፈቀደለት ለማወቅ ተችሎአል።ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አዜብ መስፍን አልወጣም ብላ የሙጢኝ ማለቷ እንደሆነ ከታማኝ ምንጮች የደረሱን መረጃዎች አረጋግጠዋል።

መለስ ዜናዊ በሞት ከተለያቸው ወዲህ በመለስ ሥም መማልና መገዘት የጀመሩት ኢህአደጋዊያን ወያኔዎች አዘብ መስፍንን ለ21 አመት ከኖረቿበት ግቢ በሃይልም ሆነ በሥነሥር ዓት ለማስወጣት ድፍረት ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ ባይጠበቅም እራሷ አዜብ መስፍን ሃሳቧን ለውጣ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ብትሆን በመጀመሪያ ቀን የጠቅላይ ምንስቴርነት ንግግሩ " ዘላልማዊ ግርማና ሞገስ ለታላቁ መሪያችን ይሁን " በማለት አምልኮ መለስ የጀመረው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ለዚህ ማዕረግ ያበቃው አለቃው ምስቲ በወጣችበት ቤት ውስጥ ገብቶ ለመኖር ድፍረትና ወኔው ይኖራዋል ወይ የሚል ጥያቄ አስነስቶአል።

አዘብ መስፍን መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ከመቶ ሚሊዮን በላይ የመንግሥት ገንዘብ ወጪ በማድረግ ምንሊክ ቤተመንግሥት ውስጥ እያሳነጻ መሆኑ ተዘግቦ ወደ ነበረው ህንጻ እንድትዛወርና አሮጌውን ህንጻ ለሃይለማሪያም ደሳለኝ ልትሰጠው እንደምትችል ለቤተመንግሥቱ ቅርብ የሆኑ አንድ ምንጭ ለዝግጅት ክፍላችን ፍንጭ ሰጥተዋል።

አዜብ መስፍን የባሌበቷን ሥልጣን መከታ በማድረግ በዘረፈቺው የአገር ሃብትና ገንዘብ አገሪቱ ውስጥ አትራፊ በሚባሉ የንግድ ድርጅቶች ሁሉ ውስጥ እጇን አስገብታ በብርሃን ፍጥነት ለመክበር ከበቁ ጥቂት የዘመኑ የናጠጡ ዲታዎች ተርታ መሰለፏን ከአመት በፊት ስፔን ውስጥ የሚታተም ጋዜጣ ዘግቦ እንደነበር አይዘነጋም።

## የአማራ ክልል ወጣት ማህበር ፕሬዚዳንት ወያኔን በሀይል ለማስወገድ የሚደረገዉን ትግል ለመቀላቀል ትግል ሜዳ መግባቱን አስታወቀ

የኢህአዴግ አባልና የአማራ ክልል ወጣት ማህበር ፕሬዚዳንት የነበረዉ ወጣት ዘመነ ካሴ የወያኔን ዘረኛ ስርአት ማስወገድ የሚቻለዉ በሀይል ነዉ በማለት ከተከታዮቹ ጋር ጫካ ገብቶ ትግል የጀመረ መሆኑን ለኢሳት ቴሌቪዥን በሰጠዉ ቃለመጠይቅ ገለጸ።

ወያኔ ስልጣን ይዞ በቆየባቸዉ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ዉስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ የተረፈዉ ነገር ቢኖር ዘረኝነት፤ማንአለብኝነትና ንቀት ብቻ ነዉ ያለዉ ወጣት ዘመነ ካሴ የኢትዮጵያ ወጣት ከአሁን በኋላ እንደዚህ አይነት ዉርደት የሚቀበልበትና በገዛ አገሩ የበይ ተመልካች የሚሆንበት ግዜ አክትሟል ብሏል። ወጣት ዘመነ ከኢትዮጵያ ሲወጣም ሆነ የትግል ሜዳ ሲገባ ብዙ ተከታዮች እንዳሉት ገልጾ አሁንም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ግዜ ሁሉ የኢትዮጵያ ወጣት በተለይ እሱ በፕሬዚዳንትነት ይመራዉ የነበረዉ የአማራ ክልል ወጣት አብሮት ለመታገል ዝግጁ እንደሆነ ገልጿል።

ወጣት ዘመነ ኢትዮጵያ ዉስጥ በነበረበት ወቅት ከመኖሪያ ቤትና መኪና ዉጭ ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚከፈለዉና ብዙ ጥቅማጥቅሞችም ያገኝ እንደነበር ገልጾ ለትግል ያነሳሳዉና ወያኔን በኃይል እንዲፋለም የገፋፋዉ የራሱ ሁኔታ ሳይሆን በኢትዮጳያ ህዝብ ላይ የሚደርሰው ከፍተኛ በደል እንደሆነ ተናግሯል። የኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ አጥቶ ሲሰቃይና ወጣቱ ህብረተሰብ የወደፊት ተስፋዉ ጨልሞ ከአገር ሲሰደድ እየተመለከተ እሱ ወያኔ በሰጠዉ ቤትና መኪና ተንደላቅቆ መኖር ሂሊናዉ እንዳልፈቀደለት የተናገረዉ ወጣት ዘመነ ከአሁን በኋላ ወያኔ እስካልተወገደ ድረስ እረፍት እንደማይኖረዉ አስታውቆአል።

ወጣት ዘመነ ከወያኔ ኢህአዴግ ጋር በሰራባቸው ወቅቶች የድርጅቱን ጸረ ህዝብና ጸረ አገር አቋም ጠንቅቆ የማወቅ ዕድል እንዳገኘ ገልጾ የኢትዮጵያ ወጣት በወያኔ አሸከርካሪነት ከሚዘወረው ኢህአደግ ከአሁን በኃላ ምንም ነገር እንዳያጠብቅና ይልቁንም ወያኔንም ሆነ ወያኔን ተሸክሞ የሚዞረዉን ኢህአዴግን ጠራርጎ ከሥልጣን ለማስወገድ በሚደረገዉ ትግል ወጣቱ ግንባር ቀድም ሚና እንዲጫወት ጥሪዉን አስተላልፏል።

## ኢትዮጵያዉያን የህግ ባለሙያዎች የኃይለማሪያም ደሳለኝ ሹመት የአገሪቱን ህግና ስርአት የተከተለ አለመሆኑን አጋለጡ

ባለፈዉ አርብ መስከረም 11 ቀን 2005 ዓም የ ሀይለማሪያም ደሳለኝን የጠ/ሚኒስትርነት ሹመት ለማጽደቅ በአስቸኳይ የተሰበሰበዉ የወያኔ ፓርላማ የተከተለዉ አሰራር የአገሪቱን ህገመንግስትም ሆነ የፓርቲዉን ስርዐት የጣሰ አሰራር ነበር ሲሉ በጉዳዩ ላይ እዉቀት ያላቸዉ የህግ ባለሙያዎች ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 73 ንዑስ አንቀጽ አንድ ጠ/ሚኒስትሩ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት መካከል ይመረጣል የሚል ቢሆንም በተጨባጭ እንደታየዉ ግን ጠ/ሚኒሰትሩን የመረጠዉ ኢህአዴግ ሲሆን ፓርላማዉ ተሰብስቦ የፓርቲዉን ምርጫ ከማጽደቅ ዉጭ ህገ መንግስታዊ ተግባሩን በተመለከተ ምንም የሰራዉ ስራ የለም።

በሌላ በኩል ደግሞ እስካሁን ድረስ ኢህአዴግ በተከተለዉ አሰራር የአገሪቱን ምክትል ጠ/ሚኒስትር የሚሰይመዉ ጠ/ሚኒስትሩ ሲሆን ኃማሪያም ደሳለኝ ይህንን ስልጣን አለማግኘቱ ከዚህ ቀደም መለስ ዜናዊ የሰራቸዉን ስራዎች ሁሉ መስራት መቻሉን ከአሁኑ አጠራጣሪ እየሆነ መጥቷል ሲሉ የህግ ባለሙያዎቹ ተችተዋል።

ከሰሞኑ የኢህአዴግ ፓርቲ ያሳየዉ ማን አለብኝነትና ፓርላማዉ ያሳየዉ ንዝህላልነት እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነዉ ያሉት የህግ ባለሙያዎቹ ኢህአዴግ የአገሪቱን ጠ/ሚኒስትርና ምክትል ጠ/ሚኒስትር መምረጡ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን መሪ የሰልጣን ዘመን በመገደብም በህግ የተደነገገለትን የህግ አስፈጻሚነት ብቻ ሳይሆን የህግ አዉጭነት ሚናም ተጫዉቷል ብለዋል። አዲስ አበባ ዉስጥ በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወረ የህዝብ አስተያየት የሰበሰበዉ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ በላከልን ዘገባ መሰረት ብዙ አትዮጵያዉያን ኢህአዴግ የራሱን ፓርቲ አባላት የስልጣን ዘመን እንጂ የአገሪቱን መሪ የስልጣን ዘመን የመወሰን መብት ማን ሰጠዉ ሲሉ ጠይቀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን የኃይለማሪያምን ሹመት አስመልክታ ባሰተላለፈችዉ የደስታ መግለጫ መልዕክት የኃይለማሪያምን ሹመት የሚያወሳ ሳይሆን የሟቹን የመለስ ዜናዊን ስራ የሚያወዳደስ፤ ሰሚዉን ግራ የሚያጋባና የተሿሚዉን ሰዉ ክብር የሚነካ መግለጫ በማዉጣት ቤተክሪስቲያኒቱ አሁንም በወያኔ የፖለቲካ መሪዎች የምትዘወር መኪና መሆኗን አሳይታለች። አዲሱን ጠ/ሚኒስትር እንኳን ለዚህ አበቃዎት የሚል የደስታ መግለጫ ማስተላለፏንና መልካም የስራ ዘመን መመኘቷን ትታ የሟቹን ጠ/ሚኒስትር ታላቅነትና የስራ ብቃት ብቻ መዘርዘሯ ቤተክርስቲያኒቱ ጉዳይዋ ከአገር ጋር ሳይሆንና ከአንድ ጎሳ ወይም ግለሰብ ጋር መሆኑን ያሳይል ሲሉ ብዙዎች ትችታቸዉን ሰንዝረዋል።

## በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ሞት ተደስታችኋል የተባሉ 120 የመተማ ነዋሪዎች … (ከገጽ 1 የዞረ)

የመለስ ዜናዊን ሃዘን በየክልሉ ለማስተባበር በሃላፊነት ተመደበው ከነበሩት አንዱ ለኢሳት ሲገልጽ ወረዳዎች በግምገማ ከሚደርስባቸው መከራ ለመገላገል የተሻለ ለቅሶ ለማሳየት ፉክክር ውስጥ ገብተው እንደነበርና በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው የተሰራጩ “አባይን የደፈረ መሪ ፣ እኩልነትንና ፍትህን ያሰፈነ መሪ፤ ለአገር ዕደገትና ልማት ስሯሯጥ ለራሱ ጊዜ ያልነበረው መሪ” የሚሉ መፈክሮችን ከፍ አድርጎ የማስተጋባት ቲያትር ሲሰራ ሰንብቶአል ብሎአል። በጎንደር የሃዘን አስተባባሪ ሆነው ግዳጃቸውን የተወጡ የኢሳት ምንጭ እንደገለጹት ለሀዘን የወጣው ህዝብ ሀዘኑን ገልጦ ሲጨርስ ከ64 እስከ 700 ብር እንደተከፈላቸውና ክፍፍሉ ላይ በተፈጠረው መበላለጥ የየወረዳው ካቢኔ አባላት ሲወዛገቡ ሰንብተዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org